# አዲስ ዘመን ከአዲስ ልብ ጋር !

ነሐሴ 28 1999 ዓ.ም

በቅድሚያ በአገር ዉስጥና ከአገር ዉጭ ለምትኖረዉ ኢትዮጵያዊ ወገኔ ሁሉ መልካም እንቁጣጣሽ- መልካም ሚሌኒየም እመኝልሃለሁ !

ኢትዮጵያን በጽጌረዳ አበባ እመስላታለሁ። ጽጌሬዳ አበባ በጣም ተወዳጅ የሆነች አበባ ናት። ብዙ ጊዜ በማስቀመጫ ዉስጥ ተደርጋ የሚመጡ እንግዶች እንዲያይዋት በሚታይ ቦታ ትቀመጣለች። የክብር የፍቅርና የዉበት ምልክት ናት። ኢትዮጵያ አገራችንም በነጻነቷና በአንድነቷ ታፍራና ተከብራ የኖረች፣ ከተለያዩ ብሄረሰቦች የተወጣጡ ልጆቿ ዉበቷ የሆኑላት፣ ለኢትዮጵያዉያን ብቻ ሳይሆን ለጥቁር ህዝብ ሁሉ ኩራት የሆነች አገር ናት።

የቀድሞዉ የደቡብ አፍሪካ ፕሬዘዳንት ኔልሰን ማንዴላ ስለ ኢትዮጵይ ሲናገሩ *“ኢትዮጵያ በሐሳቤ ልዩ ቦታ አላት፤ ኢትዮጵያን መጎብኘትም ፈረንሳይ እንግሊዝንና አሜሪካን ከመጎብኘት የበለጠ ይሰበኛል”* ይሉናል። ስለ ዳግማዊ አጼ ሚኒሊክ አንድ በተባበሩት መንግስታት ጽ/ቤት የኢኮኖሚክ ኮሚሽን ፎር አፍሪካ ከፍተኛ ባለስልጣን የነበሩ ሴኔጋላዊ ከ አሥራ አምስት አመታት በፊት የነገሩኝ አንድ ቁም ነገር ነበር። *“ስለ ሚኒሊክና የአድዋዉ ጦርነት የሴኔጋል ተማሪዎች በትምህርት ቤት ይማሩታል። የአድዋዉ ድል የአፍሪካ የነጻነት ምዕራፍ ጅማሬ ነዉ። ሚኒሊክ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ አባት ናቸዉ”* ሲሉ ነበር ኢትዮጵያ በሴነጋል ተወላጆች ዘንድ ያላትን ልዩ ቦታ በግልጽ ያስቀመጡልኝ። **አዎ ኢትዮጵያ የኛ የኢትዮጵያዉያን ብቻ ሳይሆን የጥቁር ሕዝብ ሁሉ ጽጌሬዳ ናት።**

ኢትዮጵያ እንዲህ ለጥቁር ሕዝብ ሁላ ኩራት የሆነችዉ በቀላሉ አይደለም። የኢትዮጵያን ነጻነትና ክብር ለማስጠበቅ ትለቅ መስዋዕትነት ስለተከፈለ ነዉ። ከጥቂት ቀናት በኋላ 1999 ዓ.ምን ጨርሰን 2000 ዓ.ም እንጀምራለን። ሁላችንንም በሰላምና በጤና ጠብቆ ሰለዚህ ያደረሰን አምላክ ስሙ ከዘላለም እስከ ዘለላም የተመሰገን ይሁን።

ወደ አዲሱ ዘመንና አዲሱ ሚሌኒየም ስንሸጋገር፡

- በአድዋ፣ በማይጨዉ፣ በአዱሊስ በወልወልና በመላዉ የኢትዮጵያን ግዛት ከወራሪ ጣሊያኖች ጋር፤ በጉንደትና በጉራ ከግብጾች ጋር፤ በአፋር ምድር ከቱርኮች ጋርና እንዲሁም “ታላቋ ሶማሊያ” በሚል መርህ የተሰማራዉን የዉጭ ወራሪ ኃይል ለመመከት በሃረርጌ በተደረጉት ታላቅ ትንቅንቆች የተከፈለዉን የደም መስዋዕትነት እያሰብን ነዉ።
- በመተማ ከደርቡሾች በተተኮሰ ጥይት ያለፉትን አጼ ዮሐንስ አራተኛ፣ በመቅደላ ተራራ ለኢትዮጵያ ክብር ሲሉ እጃቸዉን ለእንግሊዞች ላለመስጠት የራሳቸዉን ጥይት የጠጡትን መይሳዉ አጼ ቴዎድሮስን ፣ የዘርዓይደረሰን፣ የአብዲሳ አጋን፣ የደጃች ባልቻ አባነፍሶን፣ የፊታዉራሪ ገበየሁን፣ የጥቁር አንበሳ ጀግኖችንና እንዲሁም በተለያዩ አጋጣሚ ለኢትዮጵይ ነጻነትና ክብር ሲሉ ህይወታቸዉን ሰዉተው ያለፉ ወገኖቻችንን ታላቅ ስራ በመዘከር ነዉ።

ጽጌሬዳ መልከ መልካምና ያማረች የሆነችዉን ያህል የሚዋጉና የሚያደሙ እሾሆችም አሏት። በአዲስ አበባ፣ በሃዉሴን፣ በአሲምባ፣ በከረን፣ በአስመራ፣ በአሶሳ፣ በጎንደር፣ በኦጋዴን፣ በምዕራብ ወለጋ፣ በበደኖ፣ በአርባ ጉጉ ... በእሾህ ተወግቶ የስንቱ ኢትዮጵያዊ ደም ፈሰሰ ? ስንቱ በወንድሙ እጅ ታረደ ? የስንቱ ወጣት እናት ልጇን አጣች?

ትዝ ይለኛል የአንደኛ ክፍል ተማሪ ሳለሁኝ አዲስ አበባ አራተኛ ክፍለ ጦር (መሻለኪያ ሰፈር) አካባቢ በተነሳዉ የተኩስ ልውውጥ በጥይት ተመተዉ የወደቁ አራት ወጣቶች። ትዝ ይለኛል ከአሥራ ዘጠኝ አመታት በፊት አስመራ በሚታተም አንድ ጋዜጣ ላይ ታትሞ የነበረ ፎቶግራፍ። በዚህ ፍቶግራፍ የሰዎች ሬሳ ተሰብስቦ እንደ ተራራ ተከምሮ ነበር። የዚያን ሰሞን አፋቤት የምትባለዉን ትንሽ ከተማ ሻቢያ ተቆጣጠረ። በቀጣይነት የከረን ከተማን ለመያዝ በተደረገዉ ሙከራ የሞቱት የሻቢያ ወታደሮች ነበሩ በጋዜጣዉ ላይ ሬሳቸዉ የታየዉ። የዚያን ጊዜ በአላማቸዉ ባንስማም የኛ ወገኖችና ወንድሞቻችን ነበሩ። ትዝ ይለኛል በ 1991 ዓ.ም ኢሕአዴግ አዲስ አበባን በተቆጣጠረ በሁለተኛዉ ቀን የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የተቃዉሞ ሰልፍ ሲደረግ። እስቲፋኖስ ቤተ ክርስቲያን (መስቀል አደባባይ ) ሰልፈኛዉ ሲደርስ ተኩስ ተጀመረ። ከሃያ ዘጠኝ በላይ ወጣቶች ተገደሉ። **አይ አንቺ እማማ ኢትዮጵያ - የደም መሬት !!!**

እነዚህ ሁሉ ያለቁት ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ተምረዉ፣ ትዳር ይዘዉ፣ ልጆች ወልደዉና ከብረዉ ለወግ ለማዕረግ መድረስ የሚችሉ ነበሩ። አሁን በሕይወት እንዳለን እንደ ማናችንም አንዳንዶቹ ሀኪሚች፣ አንዳንዶቹ መሃንዲሶች፣ አንዳንዶቹ ምሁራን፤ አንዳንዶቹ የሕግ ባለሞያዎች ሆነዉ ህብረተሰባቸዉንና አገራቸዉን ሊጠቅሙ የሚችሉ ነበሩ። ታዲይ ምን ያደርጋል የኢትዮጵያ ኋላ ቀር የደም መፋሰስና የመገዳደል ባህል ሰለባ ሆነዉ ቀሩ።

ወደ አዲሱ ሚሊየነም ስንሸጋገር በአኩሪ ታሪካችን እንደምንኮራዉ ሁሉ በአሳፈሪዉ ታሪካችንም ማፈር አለብን። አገር እያለን ተሰደናል። ወገን እያለን ብቸኞች ሆነናል። ለሌሎች አገሮች የተረፈ ታላላቅ ወንዞች እያሉን ተጠምተናል። ምግብ እያለን ተረበናል። የአገራችን መሬቶች በደም ከመራሳቸዉ የተነሳ እህል ማብቀል አቁመዉ ከአመት እሰከ አመት ለህልዉናችን የፈረንጆችን እጅ እየጠበቅን ኖረናል። (ስንዴና እሩዝ ዘይትና ብስኩት እየለገሱን)

ታዲያ ለዚህ ሁሉ መከራና የሰቆቃ እሽክርክሪት ተጠያቂዉ ማን ሊሆን ይችላል ? አንዳንዶቻችን በአገራችን ለተፈጠረዉ ችግርና መከራ እጆቻችንን መንግስት ላይ እንቀስራለን። በንጉሱ ዘመን የዓጼ ሃይለስላሴ ቀዳማዊን አገዛዝ ስንረግምና ስንቃወም አብዮቱ ፈነዳ። "ኢትዮጵያ ትቅደም ያለ ምንም ደም" ተብሎ ተለፈፈብን። ወታደራዊዉ መንግስት ዙፋኑን በልጆቻችን አስክሬን ላይ ሰርቶ ገዛን። ከዚያም ቁምጣ የታጥቁና ከደርግ ብሶት የተወለዱ "ነጻ ልናወጣችሁ፣ ዲሞክራሲ ልናመጣላችሁ ነዉ" ብለዉ መጡ። የከተሞቻችንን በሮች ከፍተን አስገባናቸዉ። ብዙም የተሻለ ነገር አልመጣም። አገር ወደብ አልባ ሆነች። ሃብት በጥቂቶች ተመዘበረ። ህዝብን በጎሳና በዘር ለመከፋፈል ተሞከረ። በዲሞክራሲ ስም ከአንድ በመቶ በታች የሆኑት ጨረቃ ላይ ሲመጠቁ ዘጠና ዘጠኝ በመቶ የሆነዉ ህዝባችን ቁልቁል ወረደ። ለመጀመሪያ ጊዜ የዲሞክራሲ ባህል አስተዋወቁን። ነጻ ጋዜጦች መዉጣት ጀመሩ። በኢትዮጵያ ታሪክ ያልታየ የሕዝቡን ቀልብና ልብ የሳባ ምርጫ ተደረገ። በርካታ ትምህርት ቤቶች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ መንገዶች ተሰሩ። "አሁንስ የብርሃን ጭላንጭል እያየን ነዉ" ብለን ልባችን በተስፋ ተሞላ። ነገር ግን ተመልሶ ጨለመ። የወንድሞቻችንም ደም መፍሰሱን ቀጠለ።

**አዎን - በኢትዮጵያ ለተፈጠረዉ ችግር ዋነኛዉ ምክንያት የመልካም አስተዳደር ጉድለትና የህግ የበላይነት አለመኖር መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነዉ።**

ነገር ግን በዚህ ጽሁፌ ከመንግስት ሌላ መጠየቅ ያለበት አካል እንዳለ ለማሳየት እሞክራለሁ። ይህም አካል እኔና እናንተ ነን። እያንዳንዳችን ለኢትዮጵያ አገራችን ድህነትና መቆርቆዝ በርግጥ ተጠያቂ እንደሆንን ማወቅና መቀበል ይኖርብናል። ሁላችንም መጠኑ ይለያያል እንጂ አገራችንና ወገናችንን ጎድተናል። ጥይት ላንተኩስ እንችላለን። ነገር ግን ወንድሞቻችን ሲገደሉ ዝም ማለታችን እራሱ ተጠያቂ ያደርገናል።

መተሳሰብና መደጋገፍ እንደሚያስፈልግ ለማስረዳት፡ *"አሁን አንድ ኢትዮጵያዊ ጂንስ መልበስ አለበት ? ካኪ አይለብስም ። ዊስኪስ መጠጣት አለበት ? ጠጅ አይጠጣም"* ብሎ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢንጂነሪንግ ፕሮፌሰር የነበረ አንድ ምሁር ከ አሥር አመት በፊት የተናገረዉ ቁም ነገር ትዝ ይለኛል። ብልጽግና፣ ሃብትና መሻሻል መልካም ነገር ነዉ። ግን ከራሳችን አልፈን የወደቀዉን ሌላዉ ኢትዮጵያዊ ወገናችንን ለማንሳት እጆቻችን አጥረዉ ካልተዘረጉ ይህ የሞራል ዉድቀት አይደለምን።

በሰሜን አሜሪካ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያዊያን ይኖራሉ ተብሎ ይገመታል። በህግ አንድ ሰራተኛ በሰዓት ከ 7$ በታች አይከፈለዉም። በጣም ዝቀተኛ ደሞዝ አገኘ ቢባል አንድ ሰዉ ቢያንስ በአመት 15000$ ያገኛል ማለት ነዉ። የካናዳ ወይንም ለአሜሪካ መንግስት ቢያንስ 15% (2500$ በአመት) ግብር ያስከፍላል። በሺህ የሚቆጠሩ የተማሩ ከ50 ፣ ከ70፣ ከ100 ሺህ በላይ የሚያገኙ ኢትዮጵያዉያን አሉ። በንግዱ ሥራ ተሰማርተዉ የከበሩና በርካታ ሱቆችና ኢንቨስትመንቶች ያሏቸዉም የሚናቁ አይደሉም።

እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በቀን አንድ ዶላር ለኢትዮጵያ ቢለይ በአመት 365 ሚሊዮን ዶላር ይደርሳል። በዚህ ገንዘብ በአየር ጠባይ መለዋወጥ በየጊዜዉ ለረሃብ የሚጋለጠዉን ወገናችንን የፈረንጆችን እጅ ሳንጠብቅ ማዳን እንችል ነበር። ታዲያ አሁንም የነጮች ጥገኛ መሆናችን መንፈሳዊ ክስረታችንን አያሳይምን? በአገራችን ላለዉ ድህነት ተጠያቂዎች አያደርገንምን ? ለካናዳና ለአሜሪካ 15% ከከፈልን ወገኖቻችንን ከረሃብ ለማዉጣትና ኢትዮጵያ በረሃብ ምሳሌነት እንዳትጠቀስ ለማድረግ ከደሞዛችን ከ 0.3 % በታች መክፈል ያቅተናል?

እኛ ኢትዮጵያዉያን ከቻይናዎች፤ ከጃፓኖችና ከነጮች በምን እናንሳለን ? አገራችንስ የተፈጥሮ ሃብት ከማናቸዉም ባላነሰ መልኩ እግዚአብሄር የቸራት አይደለችምን ? በአለም የተደነቁ ምሁራን፣ ሳይንቲስቶች፤ የሕግ ባለሞያዎች፣ መሃንዲሶች፣ ሃኪሞች ያሏት አገር ሆና ኢትዮጵያን ከድህነቷ ማንሳትና መቀየር እንዴት ያቅተናል?

**መልሱ "አያቅተንም" ነዉ። ዶ/ር በፈቃዱ ደግፌ በቅርብ ጊዜ ዉስጥ በስዊድን ለሚገኝ የሬዲዮ ጣቢያ እንደተናገሩት *"ኢትዮጵያን የተቸገሩና የተጨቆኑ ከእርሷ የሚሸሹ ሳይሆን ወደ እርሷ የሚሸሹ እናደርጋታለን፤ ይቻላል*" እንዳሉት ኢትዮጵያን የአፍሪካ ጃፓን ማድረግ ይቻላል። የሚያስፈልገዉ አንድ ነገር ብቻ ነዉ። እርሱም ፍቅርና መተሳሰብ ነዉ።**

ሐዋርያዉ ቅዱስ ጳዉሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈዉ መልእክቱ የፍቅርን ትርጉም ይሰጠናል። *"ፍቅር ይታገሳል፣ ቸርነትንም ያደረጋል፤ አይቀናም አይመካም አይታበይም፤ ፍቅር የማይገባዉንም አያደረግም፣ የራሱንም አይፈልግም፤ ፍቅር አይበሳጭም በደልንም አይቆጥርም፤ ከእዉነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ሰላ አመጻ ደስ አይለዉም .."* በማለት በዝርዝር አስተምሯል።

ፍቅር ካለን አንዳችን በአንዳችን ላይ በበቀል በእልህና በጭካኔ አንነሳም። ፍቅር ካለን ያለፈዉን መጥፎ ታሪካችን ላይ ብቻ "እኝ" ብለን ልባችንን ለእርቅና ለይቅርታ አንዘጋም። ፍቅር ካለን በወንድማችን እሬሳ ላይ እየተረማመድን በደም የተገኘ ሃብት አናከማችም። ፍቅር ካለን ጉንበስ ብለን የወንድማችንን እግር እናጥባለን እንጂ በባዶ ትዕቢት አንሞላም። ፍቅር ካለን ያለችንን አንድ ዳቦ ግማሹን ቆርሰን ለተራበዉ ወንድማችን እናካፍላለን። ፍቅር ካለን በሚሊዮን የሚቆጠር ወገናችን የሰቆቃ እንባ እያለቀሰ በዳንኪራና በጨዋታ ንዋያችንን አናጠፋም።

በኢሊኖይ ዊተን ከተማ የሚኖር አንድ ኢትዮጵያዊ በቅርቡ በአካባቢዉ የሚኖሩ የዉጭ አገር ተወላጆችን በማስተባበር ከ 80 ሺህ ዶላር በላይ የሚሆን ገንዘብ አሰባስቦ ነበር። በተሰበሰበዉም ገንዘብ ከመቀሌ ከተማ ወጣ ብላ የምትገኝ አይናለም ተብላ በምትታወቅ ትንሽ መንደር የሶላር ቴክኖሎጂ እቃዎችን ከጃፓን አስገብቶ መብራት ያልነበረዉ የአይናለም ነዋሪ መብራት እንዲያገኝ አስደረገ። ይህ የድሃ ወገናችንን ህይወት ለማሻሻል የሚደረግ የፍቅር ሥራ ነዉ።

"ቡክስ ፎር አፍሪካ" ከሚባለዉ ድርጅት ጋር በመተባበር የወገናችን የእዉቀት አድማስ እንዲሰፋ በሁለት ኮንቴነር ሙሉ መጽሃፍት በደሴና በአዋሳ ላሉ ትምህርት ቤቶች እንዲደርሳቸዉ ያስደረገ አንድ ኢትዮጵያዊ አዉቃለሁ። ይህ የድሃ ወገናችንን ህይወት ለማሻሻል የሚደረግ ሌላ የፍቅር ሥራ ነዉ።

የተወለደባትን የአርሲ መንደር ሲጎበኝ ምንኛ ወገኖቹ መጎሳቆላቸዉን ያየ አንድ ኢትዮጵያዊ በቅርቡ የሚኖርበትን ቤት ሸጦ በአርሲ ትምህርት ቤት ማቋቋሙ ፍቅር ዜጎችን ከተቆጣጠረ ተዓምር ማድረግ እንደሚቻል የሚያሳይ አንድ ትልቅ ምሳሌ ነዉ።

በአዲስ አበባ በአንድ ትምህርት ቤት ዉስጥ የስዕል አስተማሪ የሆነች አንዲት ወጣት የእርሷ ቢጤዎች በየመንገዱ ልጆቻቸዉን ይዘዉ ሲንከራተቱ ማየቷ እንቅልፍ አሳጥቷት "የእነዚህ የጎዳና ተዳዳሪ ልጆች የእኔ ልጆች ቢሆኑ ዝም እላቸዋለሁን ? " በሚል በተቀደሰ ሃሳብ ሕጻናትን አሰባስባ ለማስተማርና ለመመገብ ያደረገችዉን ጥረት እግዚአብሄር ባርኮላት አሁን በሽሮ ሜዳ፣ በፒያሳና በ በቦሌ መጠነኛ ህጻነ መዋያዎችን መስርታ ከመቶ በላይ ለሆኑ ሕጻናት ተስፋ ሆናለች። ይህ የድሃ ወገኖቻችንን ህይወት ለማሻሻል የሚደረግ የፍቅር ሥራ ነዉ።

**እንግዲህ አስቡት - ከላይ እንደጠቀስኳቸዉ ኢትዮጵያዉያን ሁላችንም እራሳችንን ለፍቅር ብናስገዛ የት መድረስ በቻልን ነበር ?**

"ፍቅር ከወዴት ትመጣለች ?" የሚል ጥያቄ ሊጠየቅ ይችላል። መልሱ ግልጽና ቀላል ነዉ። ፍቅር የፍቅር አምላክ ከሆነዉ ከእግዚአብሄር ዘንድ ብቻ ትገኛለች። መጽሐፍ እንደሚል እግዚአብሄር እራሱ ፍቅር ነዉ።

አሜሪካኖች አገራቸዉን የመሰረቱት በእግዚአብሄር ላይ ነዉ። የሚጠቀሙበትን ገንዘብ አገላብጠን ብንመለከት እንኳን "በእግዚአብሄር እናምናለን" የሚለዉ አረፍተ ነገር ተጽፎበታል። በእርሱ ላይ ተመስረተዋልና እግዚአብሄርም ባረካቸዉ።

እኛ ኢትዮጵያዊያን በጣም ሃይማኖተኞች ነን። ነገር ግን ሃይማኖተኝነታችን ብዙዉን ጊዜ በዉጭ ብቻ ነዉ። መንፈሳዊ አባቶቻችን በአንድ ጎን እየተራገሙና እየተወጋገዙ ሰጋ ወደሙን ይዘዉ ይቀድሳሉ። *"ይህ ህዝብ በከንፈሩ ያከበረኛል ፤ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነዉ"* ተብሎ እንደተጻፈ በከንፈራችን እንጂ በልባችን እግዚአብሄርን አልፈለግነዉም። በከንፈራችን ፍቅርን እናወራለን ልባችን ግን በጥላቻና በቂም የተሞላ ነዉ። ታዲያ እግዚአብሄር እንዴት አደርጎ ይታረቀን ?

እግዚአብሄር ሊባርከን፣ ሊያድሰንና ሊጎበኘን የታመነነ ጻድቅ ነዉ። በግላችን በቤተሰባችንና በአገራችን መጀመሪያና ተቀዳሚ ካደረግነዉና "በእግዚአብሄር እናምናለን" የሚለዉን ቃል በልባችን ካተምን የፍቅር መንፈስ በምድራችን ይፈልቃል። ፍቅሩም እንድንተቃቀፍ፤ እንድንሳሳም፤ እንድነሸካከም ያደርገናል።

በትንቢተ ሕዝቄል *"አሮጌዉንና የደነደነዉን ልብ አውጥቼ አዲስን ልብ እሰጣቹሃለዉ"* ተብሎ እንደተጻፈ ፡

- ወደ ፍቅር፣ ወደ እርቅ፤ ወደ ቅንነት፣ ወደ መተቃቀፍና ወደ ንግግር እንዲመጡ ለኢሕአዴግ ባለሥልጣናት፣ ለቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ አመራር አባላት፣ ከግፍ የተነሳ ጠመንጃ አንስተዉ እየተንቀሳቀሱ ያሉ ድርጅቶችን (ኦነግ፣ የአርበኞች ግንባር፣ የኢጋዴን ነጻ አዉጭ ግንባር ..) ለሚመሩ፣ አስመራ ለተቀመጡ ገዢዎችና የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ለሁኑ፣
- የጣሉትን የሞራል ኦቶሪቲ መልሰው እንዲያነሱ፣ እርከሰትን ከእግዚአብሄር ቤት እንዲያስወጡና እነርሱም እራሳቸዉ ወደ እርቅና ወደ አንደነት እንዲመጡ ለሃይማኖት አባቶች፣
- ከወሬና ከመጠላለፍ፣ ከግዴለሽነትና በኢትዮጵያ ላይ ተስፋ ከመቁረጥ ራሱን አዉጥቶና ፊቱን ወደ አገር ቤት አዙሮ የድሃዉን ወገናችንን ህይወት ለመቀየር በተጫባጭነት ቆርጦ እንዲነሳ በአለም ዙሪያ ተሰዶና በአንጻራዊነት በአገር ቤት ካለዉ ወገናችን የተሻለ ኑሮ ለሚኖረዉ ኢትዮጵያዊ፣
- ያለችዉን ጥቂቷን በጋር አብሮ እንደሚገብና የበለጠ እንዲተቃቀፍ በኢትዮጵያ ዉስጥ በገጠርና በከተማ ለሚኖረዉ ህዝባችን፣

እግዚአብሄር አዲስና በፍቅር የተሞላን ልብ ይስጥልን። መጪዉ ዘመን ከሞያሌ እስከ ራስ ካሳር፣ ከወልወል እስከ አሶሳ ሕዝባችን በሰላምና በመፈቃቀር የሚኖርበት፣ የአገራችንን የተፈጥሮ ሃብት በአግባቡ የምንጠቀምበትና የተሰደዱ ኢትዮጵያዉያን ከካሊፎርኒያ ወደ ድሬደዋ፣ ከቺካጎ ወደ ጎንደር፣ ከዳላስ ወደ መቀሌ፣ ከለንደን ወደ አስመራ፣ ከአትላንታ ወደ ያቤሎ፣ ከበርሊን ወደ ጅጅጋ፣ ከሲታያትል ወደ ነቀምቴ፣ ከሜኔሶታ ወደ ደሴ፣ ከዲሲ ወደ ጋምቤላ፣ከሲድኒ ወደ አዋሳ፣ ከቶሮንቶ ወደ ደብረ ማርቆስ፣ከደቡብ አፍሪካ ወደ አሰላ ...የሚመለሱበት፣ ሰማይና ምድርን የፈጠረ አምላክ በእዉነትና በመንፈስ የሚመለከበት ዘመን ይሁንልን !

## አዲሱን ዘመን ፣ አዲሱን ሚሌኒየም ከአዲስ ልብ ጋር !!!!

ግርማ ካሣ
ቺካጎ (**muziky68@yahoo.com**)
+